አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

ቁጥር 25, ሰኔ 2015 ዓ.ም Issue No. 25, June 2023

# አዋሽ ዜና መጽሔት
# Awash Newsletter

በብራንዲንግና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚታተም
Published by: Branding & Communication Directorate

ዋና አዘጋጅ: ተሾመ ዋቅጅራ

ረዳት አዘጋጆች: ሰላም ተክለጽዮን
ድሪባ መገርሳ
ጋዲሳ አስፋው
ሲሳይ ነዳ
ዲናኦል ዱጋሳ
ጫልቺሳ ገመቹ

ፎቶግራፍ: ዳንኤል ምትኩ

EDITOR-IN-CHIEF: Teshome Wakjira
ASSISTANT EDITORS: Selam Tekletsion
Deriba Megerssa
Gadisa Asfaw
Sisay Neda
Dinaol Dugasa
Chalchisa Gemechu

PHOTOGRAPHER: Daniel Mitiku

8980
12638
www.awashbank.com
contactcenter@awashbank.com

# በዚህ እትም

አዋሽ ባንክ በሁሉም ቅርንጫፎቹ የደንበኞች ሳምንት አከበረ......1

አዋሽ ባንክ ለ2ኛ ጊዜ በግሎባል ፋይናንስ ከኢትዮጵያ ምርጡ ባንክ ተብሎ ተመረጠ ...... 4

"የ10ኛ ዙር በአዋሽ ይቆጥቡ ይቀበሉ ይሸለሙ" የሎተሪ መርኃ ግብር ባለዕድለኞች ሽልማታቸውን ተረከቡ...... 6

የታታሪዎቹ እና የቀጠሌወን የስራ ፈጠራ ውድድር አሸናፊዎች ሽልማታቸውን ተረከቡ ...... 9

የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ በተመረጡ ቅርንጫፎች እየተካሄደ ነው ...... 12

አዋሽ ባንክ አርሶ አደሮችን የብድር ተጠቃሚ የሚያደርግ አሰራር ተግባራዊ አደረገ...... 13

ባንኩ በተለያዩ ተቋማት አዘጋጅነት የተካሄዱ ኤክስፖና ባዛሮች ላይ ተሳትፎ አደረገ...... 14

ምልከታ...... 15

አንድ ለመንገድ ...... 18

# IN THIS ISSUE

Proverbs & Quotes ...... 19

Photo Reel...... 20

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# አዋሽ ባንክ በሁሉም ቅርንጫፎቹ የደንበኞች ሳምንት አከበረ




የደንበኞች ሳምንት መርኃ ግብር ማስጀመሪያ ስነ-ሥርዓት

አዋሽ ባንክ ''ለላቀ የደንበኞች እርካታ እንተጋለን'' በሚል መሪ ቃል በሁሉም ቅርንጫፎቹ ከሚያዝያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሳምንት በዓይነቱ ለየት ያለ የደንበኞች ሳምንት አክብሯል፡፡

በደንበኞች ሳምንት የማስጀመሪያ መርሐ ግብር ላይ የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሀይ ሽፈራው እንደገለጹት የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ ደንበኞችን ማመስገን፣ ማወደስና ማክበር በመሆኑ ሁሉም የባንኩ የዋና መ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች በባንኩ ቅርንጫፎች በአካል በመገኘት አገልግሎት እንደሚሰጡና የደንበኞችን ችግሮች በአካል ተገኝተው መፍትሔ በመስጠት የሕዝብ አገልጋይነታቸውን የሚያስመሰክሩበትና የቅርንጫፍ ሠራተኞችን ሞራል የሚያነሳሱበት መርኃ ግብር እንደሆነ ተናግረዋል፡፡



የደንበኞች ሳምንት አገልግሎት አሰጣጥ በከፊል

ዋና ስራ አስፈጻሚው እንደተናገሩት የደንበኞችን እርካታ በሚቀጥሉት ጊዜያቶች ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በዋናው መሥሪያ ቤት እና በሁሉም ቅርንጫፎች ያሉ ሠራተኞች ከምን ጊዜውም በላይ ተቀናጅተው እና ተባብረው ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

አቶ ፀሐይ ሽፈራው የደንበኞች ሳምንትን ምክንያት በማድረግ በቅርንጫፎች በመገኘት ለተለያዩ ደንበኞች የባንክ አገልግሎት ሲሰጡ ውለዋል፡፡ በተያያዘ ዜናም ደም የሰጡ ሲሆን የባንኩ አመራሮች እና ሠራተኞች በሁሉም ቅርንጫፎች የደም ልገሳ መርኃ ግብር ሲያደርጉ ውለዋል፡፡



የደም ልገሳ መርኃ ግብር በከፊል

በተጨማሪም ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ዘርፈ ብዙ የበጎ አድራጎት ስራዎችን በማከናወን የህዝብ አለኝታነቱን ያስመሰከረው አዋሽ ባንክ የደንበኞች ሳምንት ምክንያት በማድረግ በጌርጌሴኖን የአእምሮ ህሙማን መርጃ እና ማገገሚያ ማዕከል ለሚገኙ የአዕምሮ ህሙማን የማዕድ ማጋራት መርኃ ግብር አከናውኗል፡፡ ለዚህም መልካም አርአያ ተግባሩ ከማዕከሉ የምስጋና የምስክር ወረቀት ተበርክቶለታል፡፡




የማዕድ ማጋራት ስነ ሥርዓት



የደንበኞች ሳምንት አገልግሎት አሰጣጥ በከፊል

# አዋሽ ባንክ ለ2ኛ ጊዜ በግሎባል ፋይናንስ ከኢትዮጵያ ምርጡ ባንክ ተብሎ ተመረጠ




አቶ ዮሐንስ መርጋ ሲኒየር ቺፍ ማርኬቲንግ ኦፊሰር ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ

የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ዕድገትን በየዓመቱ በመተንተን የሚታወቀው ግሎባል ፋይናንስ ተብሎ የሚጠራው ድርጅት ለ30ኛ ጊዜ እ.ኤ.አ. የ2023 ዓመታዊ የዓለም እና የየአገሮች ምርጥ ባንኮችን ውጤት ይፋ አድርጓል፡፡ አዋሽ ባንክ ለሁለተኛ ጊዜ ከኢትዮጵያ ምርጥ ባንክ ሆኖ በብቸኝነት መመረጡን ግሎባል ፋይናንስ አስታውቋል፡፡

የአዋሽ ባንክ ሲኒየር ቺፍ ማርኬቲንግ  ኦፊሰር አቶ ዮሀንስ መርጋ እንደገለጹት አዋሽ ባንክ እ.ኤ.አ በ2023 ለሁለተኛ ጊዜ ከኢትዮጵያ በብቸኝነት የዓመቱ ምርጥ ባንክ ሆኖ በመመረጡ  ምርጫው የሀገራችንን የፋይናንስ ተቋማትን ገጽታን ከፍ የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ይፋ በተደረገው የየአህጉሮቹ ምርጥ ባንኮች ምርጫ ሂደት መሠረት ከአፍሪካ ምርጥ ባንኮች ተብለው የተመረጡት ከምሥራቅ አፍሪካ፣ ከደቡብ አፍሪካ፣ ከሰሜን አፍሪካ፣ ከማዕከላዊ አፍሪካና ከምዕራብ አፍሪካ በአጠቃላይ 36 ባንኮች ሲሆኑ ምርጥ ባንኮች ተብለው የተመረጡት በተለያዩ መስፈርቶች ቢሆኑም በዋናነት ግን የተመረጡት በሁለት መስፈርቶች ሲሆን እነሱም የባንኮቹ በዓመቱ ውስጥ ያስመዘገቡት የትርፍና የጠቅላላ ሃብት ዕድገት መጠን መሆኑ ታውቋል፡፡

አዋሽ ባንክ ከ10 ምርጥ የምሥራቅ አፍሪካ ባንኮች መካከል አንዱ በመሆን ከኢትዮጵያ ደግሞ ብቸኛ ሆኖ በመስፈርቱ መሰረት የዓመቱን ጠቅላላ ሃብት በአሜሪካ ዶላር 3.9 ቢሊዮን ከፍ በማድረጉና የዓመቱን ትርፍ ደግሞ በአሜሪካን ዶላር 137 ሚሊዮን በማድረሱ ምክንያት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ባንኩ ከዚህ በፊት ከምሥራቅ አፍሪካ ከሚገኙ 10 ምርጥ ባንኮች አንዱ ለመሆን በነደፈው ስትራቴጂ መሠረት የ2025 ዕቅዱን አስቀድሞ በመተግበሩ ምክንያት ሊመረጥ የቻለ መሆኑን አቶ ዮሀንስ ገልጸዋል፡፡

ምርጫው የተካሄደው ከ150 አገሮች በላይ ባሉ ባንኮች መካከል ሲሆን ከአፍሪካ 36 ባንኮች መመረጣቸውንና የምርጫው ዋና ዋና መስፈርቶች ባንኮቹ ያስመዘገቡት ውጤት በተለይም ትርፋማነት፣ የሀብት ዕድገት፣ ተደራሽነት፣ ለደንበኞቻቸው ያሳዩት ቅን አገልግሎት፣ ለወደፊት ስኬት አስተማማኝ መሠረት መጣልና የፈጠራ ሥራዎች ናቸው፡፡

ለአሸናፊ ባንኮች የሚሰጠው ዕውቅናና ሽልማት እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 14 2023 በሚካሄደው የዓለም የገንዘብ ድርጅት እና የዓለም ባንክ በሞሮኮ ማራካሽ በሚያደርጉት የጋራ ጉባዔ ላይ የሚሰጥ መሆኑን እና የምርጫው ዝርዝር ውጤትና መስፈርት ግንቦት ወር (እ.ኤ.አ. May 2023) በግሎባል ፋይናንስ መጽሔት ዕትም ላይ ወጥቷል፡፡

አዋሽ ባንክም በዕለቱ የዕውቅና እና የሽልማት ሥነ-ሥርዓት ላይ ሽልማቱን በክብር የሚቀበል ይሆናል፡፡

እ.ኤ.አ በ2022 አዋሽ ባንክ ከምስራቅ አፍሪካ ከተመረጡት ምርጥ ባንኮች አንዱ እንደነበረና ከኢትዮጵያ ደግሞ ብቸኛ ሆኖ የዓመቱ ምርጥ ባንክ ተብሎ መመረጡን በመግለጫው ላይ አስታውሰዋል፡፡



# “የ10ኛ ዙር በአዋሽ ይቆጥቡ ይቀበሉ ይሸለሙ” የሎተሪ መርኃ ግብር ባለዕድለኞች ሽልማታቸውን ተረከቡ



የአንደኛ ዕጣ ተሸላሚ አቶ ታስልኦች ኳንግ ቤል

አዋሽ ባንክ ለአስረኛ ዙር ያዘጋጀው የይቆጥቡ ይሸለሙ የሎተሪ ዕጣ አሸናፊ ለሆኑ እድለኞች ያዘጋጀውን ሽልማት ሚያዝያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም የባንኩ ደንበኞች እና ተጋባዥ የክብር እንግዶች በተገኙበት ለባለ ዕደለኞቹ አስረክቧል፡፡

የአዋሽ ባንክ ሲኒየር ማርኬቲንግ ቺፍ ኦፊሰር አቶ ዮሀንስ መርጋ  በሽልማት ስነ ሥርዓቱ ላይ የአዋሽ ባንክ ይቆጥቡ ይሸለሙ መርኃ ግብር በዋናነት ለሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት በጣም አስፈላጊ እና ወሳኝ የሆነውን ቁጠባ እና የውጭ ምንዛሪ በማሳደግ ረገድ የራሱን አስተዋፅኦ ለማድረግ እና በህገ-ወጥ መንገድ ወደ አገራችን የሚመጣውን የውጭ ምንዛሬ በሕጋዊ መንገድ እንዲመጣ በማድረግ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ለአገራችን ልማትና ዕድገት እንዲውል ለማስቻል ሲሆን በሌላ በኩል ከተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የተላከላቸውን የውጭ አገር ገንዘቦች በአዋሽ ባንክ በኩል የሚቀበሉ ወይም አምጥተው የሚመነዝሩ ደንበኞችን በሽልማት መልክ ማበረታቻ እንዲያገኙ ያለመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የ10ኛው ዙር ''በአዋሽ ይቆጥቡ፣ ይቀበሉ፣ ይሸለሙ'' የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ የሎተሪ መርሐ ግብርም ልክ እንዳለፉት ዘጠኝ ዙሮች በተሳካ ሁኔታ ተጠናቆ ዕጣው ታህሳስ 13 ቀን 2015 ዓ.ም በብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ በህዝብ ፊት በይፋ ወጥቷል፡፡

የተዘጋጁት የሽልማት ዓይነቶች በአራት ደረጃዎች የተከፋፈሉ ሲሆን ለአንደኛ ዕጣ የተዘጋጀው የሽልማት ዓይነት አንድ ዘመናዊ የቤት አውቶሞቢል ሱዙኪ ዲዛየር መኪና የሎተሪ ቁጥር 00021413447 የያዙት አቶ ታስልኦች ኳንግ ቤል በጋምቤላ ከተማ ጋምቤላ ኒው ላንድ ቅርንጫፍ የባንክ አገልግሎት ባገኙበት ወቅት በተሰጣቸው የሎተሪ ዕጣ ቁጥር አሸናፊ ሆነዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ለ2ኛ እጣ የተዘጋጁት (ሶስት ዕጣዎች) እያንዳንዳቸው ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ መኪኖች ጨምሮ በርካታ ባለ 43 ኢንች ኤልኢዲ ቴሌቪዥኖች እና ስማርት የሞባይል ስልክ ቀፎዎችን ዕጣ ለወጣላቸው ዕድለኞች ተበርክቶላቸዋል፡፡




የሁለተኛ ዕጣ ተሸላሚ ባለዕድለኞች በከፊል

የሎተሪው ባለዕድለኞች በበኩላቸው አዋሽ ባንክ ባበረከተላቸው ሽልማት መደሰታቸውን በመግለጽ ይህን መሰል ዕድሎችን ለተጠቃሚዎች ማዘጋጀቱ ባንኩን የሚያስመሰግነው እና ታማኝነቱን ያሳየበት በመሆኑ በቀጣይ ከባንኩ ጋር አብሮ ለመስራት የሚያበረታታ ነው ብለዋል፡፡





የሦስተኛ ዕጣ ተሸላሚዎች  በከፊል

አዋሽ ባንክ የሀገራችንን የቁጠባ ባህል ለማበረታታት እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ ‘’በአዋሽ ይቆጥቡ፣ ይቀበሉ፣ ይሸለሙ” መርሃ ግብር በተጨማሪ የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡



የአራተኛ ዕጣ ተሸላሚዎች  በከፊል

በአዋሽ ይቆጥቡ፣ ይቀበሉ፣ ይሸለሙ” 10ኛው ዙር የሎተሪ ዕጣ በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ያልተቆጠበ ድጋፍ ላደረጉት የመንግስት፣ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦችን በማመስገን መርሃ ግብሩን በተጠናከረ ሁኔታ ለማስቀጠል እየሰራ እንደሚገኝ በመጠቆም ማህበረሰቡ ቁጠባን ባህሉ ማድረግ እንደሚገባ እንዲሁም ደግሞ የውጭ አገር ገንዘቦችን በሕጋዊ መንገድ በአዋሽ ባንክ  በኩል በመቀበልና ወደ ባንኩ አምጥቶ በመመንዘር ለአገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ የዕድሉም ተጠቃሚ እንዲሆኑ አቶ ዮሐንስ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# የታታሪዎቹ' እና "ቀጠሌወን" የስራ ፈጠራ ውድድር አሸናፊዎች ሽልማታቸውን ተረከቡ




በታታሪዎቹ ውድድር አንደኛ የወጣው የአንድ ሚሊዮን ብር ተሸላሚ

አዋሽ ባንክ አዳዲስ የስራ ፈጠራ ሃሳብ ላላቸው ስራ ፈጣሪዎች ባዘጋጀው የ"ታታሪዎቹ' እና "ቀጠሌወን" የስራ ፈጠራ ውድድር አሸናፊ ለሆኑ ስራ ፈጣሪዎች ያዘጋጀውን ሽልማት ግንቦት 22 እና 24 ቀን 2015 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል የመንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች እና ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት ለአሸናፊዎቹ አስረክቧል፡፡




በቀጠሌወን ውድድር አንደኛ የወጣው የአንድ ሚሊዮን ብር ተሸላሚ

የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሀይ ሽፈራው የታታሪዎቹ ውድድር የማጠቃለያ ሥነ-ሥርዓት ላይ ባሰሙት የመክፈቻ ንግግራቸው ባንኩ ሀገርን ሊጠቅሙ የሚችሉ አዳዲስ የስራ ፈጠራ ሃሳቦችን ይዘው ነገር ግን ካለባቸው የፋይናንስ ተደራሽነት ችግር ሀሳባቸውን እውን ለማድረግ ያልቻሉ ስራ ፈጣሪዎች አስፈለጊውን የፋይናንስ ድጋፍና ተጨማሪ የክህሎት ስልጠና ማግኘት የሚችሉበትን ፕሮጀክት ቀርጾ ወደ ተግባር መግባቱን ገልጸዋል፡፡




የታታሪዎቹ አሸናፊዎች

ይህ አዳዲስ የስራ ፈጠራ ባለቤቶችን ለማበረታታት አዋሽ ባንክ የቀረፀው ታታሪዎቹ' እና "ቀጠሌወን" የሚል ስያሜ በተሰጠው የስራ ፈጠራ ወድድር ላይ ከሰባት ሺህ በላይ የሚሆኑ ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የተውጣጡ እና በተለያዩ መስኮች ፈጠራቸውን ይዘው የመጡ ስራ ፈጣሪዎች ተሳትፈዋል፡፡




የቀጠሌወን አሸናፊዎች

የ"ታታሪዎቹ" እና "ቀጠሌወን" ፕሮጀክት ላይ በርካታ ወጣቶች በመሳተፍ የቢዝነስ ሙያ ስልጠና ተጠቃሚ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ለተከታታይ ሳምንታት በፋና ብሮድካስቲንግ እና በኦቢኤን ቴሌቪዥን በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ስርጭት ሽፋን በነበረው የስራ ፈጠራ ሀሳብ ውድድር ላይም በናሙና (prototype) የተደገፈ ስራዎቻቸውን በማቅረብ ብርቱ ፉክክር አድርገዋል፡፡

ተወዳዳሪዎቹም በዳኞች ውሳኔ መሰረት ከ 1 – 6ኛ ደረጃዎች ውስጥ ለገቡ አሸናፊዎች እንደየደረጃቸው ከብር አንድ መቶ ሺ እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ተሸልመዋል፡፡ ያሸነፉበትን የፈጠራ ሀሳባቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉበት ከዋስትና ነፃ እስከ ብር 5 ሚሊዮን ብድር እንደ የፕሮጀክታቸው ሁኔታ የሚመቻችላቸው መሆኑ በዋና ስራ አስፈጻሚ ተገልጿል፡፡

በተጨማሪም ለስራ ፈጠራ ውድድሩ መሳካት ከአዋሽ ባንክ ጎን በመቆም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ላበረከቱ ተቋማትና ግለሰቦች የዕውቅና የምስክር ሰርተፊኬት ተበርክቶላቸዋል፡፡

የኮርፖሬት ማህበራዊ ኃላፊነት አካል የሆነው ስራ ፈጣሪዎችን የሚያበረታታው ይህ ፕሮጀክት በቀጣይ በተሻለ መንገድ ለማስቀጠልና አጠቃላይ ማህበራዊ ኃላፊነቱንም ለመወጣት ለወደፊቱም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አቶ ፀሀይ አስታውቀዋል፡፡

በክህሎት እና ስራ ፈጠራ ሚኒስቴር የስራ ስምሪትና ገበያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን በበኩላቸው የፋይናንስ ተቋማት በማህበረሰቡ ውስጥ የስራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸው ስራ ፈጣሪዎችን ማበረታታት እና ስራ አጥነት በመቀነስ ረገድ ጉልህ ሚና ያላቸው ሲሆን ይህ አዋሽ ባንክ የጀመረው አዳዲስ የስራ ፈጠራ ክህሎት ኖሯቸው በፋይናንስ እጥረት ወደ ፊት መውጣት ያልቻሉ ስራ ፈጣሪዎችን መደገፍ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት ያለው ዝግጁነት ትልቅ ማሳያ በመሆኑ ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ይህንን አርዓያ ሊከተሉት ይገባል ብለዋል፡፡

በሌላ ዜና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክትል ፕሬዚደንት አቶ አወሉ አብዲ አዋሽ ባንክ ለአንድ ዓመት ሲያካሄድ የነበረውን "ቀጠሌወን" የተባለው የሥራ ፈጠራ ክህሎት ውድድር የማጠቃላይ መርሃ ግብር ላይ በክብር እንግድነት ተገኝተው ለአሸናፊዎች የምስክር ወረቀትና ባንኩ ያዘጋጀውን የገንዘብ ሽልማት ሰጥተዋል፡፡

አቶ አወሉ በሽልማት ስነ ሥርዓቱ ላይ ባደረጉት ንግግር አዋሽ ባንክ በባለቤትነት የሥራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች ለማበረታታትና የሥራ ዕድል ለመፍጠር በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር በጀት በመመደብ እያደረገ ስላለው የማህበራዊ ኃላፊነት መወጣት ባንኩን አመስግነዋል፡፡

ባንኩ ለብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባሻገር የሥር ፈጠራ ክህሎትን ማበረታታቱ ለሌሎች መሰል ተቋማት ትልቅ ዓርአያ እየሆነ የመጣ ስለሆነ የክልሉ መንግስት አሰፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ከባንኩ ጋር የሚቆምና እገዛ የሚያደርግ መሆኑንም አረጋግጠዋል።




የታታሪዎቹ የሽልማት ስነ ሥርዓት ታዳሚዎችና
የክብር እንግዶች በከፊል



የቀጠሌወን የሽልማት ስነ ሥርዓት ታዳሚዎችና
የክብር እንግዶች በከፊል

ከዚህም በተጨማሪ በዕለቱ ለተሸለሙ ተወዳዳሪ ወጣቶች የፈጠራ ሃሳባቸውን ወደ ምርትና ተግባር የሚለውጡ ከሆነ የክልሉ መንግስት የማምረቻና መሸጫ ቦታ ለአሸናፊዎቹ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደሚሰጣቸው ተናግረዋል።

አዋሽ ባንክ በአርቆ አሳቢና ራዕይ ባላቸው ሰዎች የተቋቋመ ባንክ በመሆኑ በሀገራችን ካሉት የግል ባንኮች መካከል ጠንካራና በጽኑ መሠረት ላይ የተገነባ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቀጥሎ የሀገርቷ ግዙፍ የፋይናንስ ተቋም መሆኑን ጠቁመው በሀገራችን ኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የራሱን አሻራ ያኖረ መሆኑን አመልክተዋል።

የወድድሩ አሸናፊዎችን በመወከል በሥነ-ስርዓቱ ላይ ንግግር ያደረገው እጩ ዶክተር መኮንን አያኔ ገና ካሁኑ የቀጠሌወን ማህበር ማቋቋማቸውን አመልክተው ባንኩ ለአንድ ዓመት ያህል ሲካሄድ የነበረው የውድድር መርሃ-ግብር በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ መዋለ ንዋይ በመመደብ ለውድድሩ አሸናፊዎች የገንዘብ ሽልማትና ያለንብረት መያዣ ብድር ለመስጠት በመወሰኑ በማመስገን፣ ጠንክሮ በመስራትም የተጣለባቸውን ኃላፊነት እንደሚወጡ ገልጿል።

የታታሪዎቹ ውድድር አሸናፊዎች በበኩላቸው አዋሽ ባንክ ለስራ ፈጣሪዎች ባዘጋጀው ፕሮጀክት ላይ ተሳታፊ በመሆን በተበረከተላቸው ሽልማት እና ከዋስትና ነፃ የብድር አቅርቦት ስለተሰጣቸው ዕድል መደሰታቸውን በመግለጽ የተሰጣቸውን ዕድል በመጠቀም በቀጣይ ያላቸውን የስራ ፈጠራ ክህሎት የበለጠ በማዳበር የህብረተሰቡን ችግር ለመቅረፍ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት በትኩረት እንደሚሰሩ እንዲሁም ባንኩ የፈቀደላቸውን የብድር አቅርቦት ለታለመለት ዓላማ እንደሚያውሉ ተናግረዋል፡፡

# የብሔራዊ  ዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ በተመረጡ ቅርንጫፎች እየተካሄደ ነው

በአዲስ አበባ ከተማ እየተካሄደ የሚገኘውን  የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ አዋሽ ባንክ በተመረጡ ቅርንጫፎቹ እያካሄደ ይገኛል፡፡

ለምዝገባ ሂደቱ የተመረጡት ቅርንጫፎች ኮተቤ፣ ሀርቡ፣ ዋ/መ/ቤት ፣ጃክሮስ፣ መርካቶ፣ ጀሞ፣ መገናኛ እንዲሁም ፊንፊኔ ቅርንጫፍ ሲሆኑ የከተማው ነዋሪዎች  በተጠቀሱት ቅርንጫፎች በመቅረብ በመመዝገብ ላይ ናቸው፡፡

የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ሁሉም ሰው ደህንነቱ የተጠበቀ የተሟላ መረጃ እንዲኖረው የሚያደርግ ሲሆን እስካሁን ባለው የምዝገባ ሂደት በርካታ ሰዎችን መመዝገብ ተችሏል፡፡




# NATIONAL ID
# ብሔራዊ መታወቂያ

## አዋሽ ባንክ አርሶ አደሮችን የብድር ተጠቃሚ የሚያደርግ አሰራር ተግባራዊ አደረገ

አዋሽ ባንክ International Food Program Research Institute(IFPRI) ከተሰኘ የአሜሪካ የምርምር ተቋም ጋር በመተባበር ለአርሶ አደሮች ዋስትና (ኢንሹራንስ) ያለዉ የብድር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አሰራር ተግባረዊ አድርጓል፡፡

ባንኮች ለሚሰጡት የብድር አገልግሎት የሚጠይቁትን ዋስትና (ማስያዣ) ማቅረብ ባለመቻላቸው አርሶ አደሮች ከባንክ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ሳይሆኑ ቆይተዋል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን የግብርና ስራ የተፈጥሮ ጥገኛ እንደመሆኑ መጠን የሚያመርቱት ምርት በየዘመኑ በሚኖረው የዝናብ መጠን ወይንም የአየር ሁኔታ የሚወሰን በመሆኑ ባንኮች በዚህ ላይ በመተማመን ለአርሶ አደሮች ብድር ከመስጠት እራሳቸውን ቆጥበው ቆይተዋል፡፡

የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት የሚሰራው አዋሽ ባንክ አርሶ አደሮችን፣ አርብቶ አደሮችንና ከፊል አርብቶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ አዲስ የባንክ አገልግሎት በማዘጋጀት ስራ ላይ ማዋል የጀመረ ሲሆን ይህንኑ በተጠናከረ ሁኔታ ለማስቀጠል ከላይ ከተጠቀሰው የምርምር ተቋም ጋር በፈጠረው የስራ ግንኙነት በአይነቱ ልዩ የሆነ የዋስትና ሽፋን ያለው የባንክ ብድር አገልግሎት ለአርሶ አደሮች ለመስጠት በፓይለት ፕሮጄክት ደረጃ ጀምሯል፡፡

ይህንን የሙከራ ፕሮጀክት ለመስራትም በምስራቅ ሸዋ ዞን አዳማ፣ ዱግዳና ቦራ ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ወሊሶና ዳዋ ወረዳዎች ተመርጠዋል።

የምርምር ተቋሙ አዋሽ ባንክ ለሚሰጠው የብድር አገልግሎት የዋስትና ሽፋን እንዲሰጥ ከኦሮሚያ ኢንሹራንስ ጋር ስምምነት ገብቷል፡፡

ይህ የብድር አገልግሎት ለአርሶ አደሩ በቀጥታ ጥሬ ገንዘብ በመስጠት የሚከናወን ሳይሆን አርሶ አደሩ በግማሽ ሄክታር ላይ ለሚያመርተው ጤፍ ወይንም ስንዴ የሚያስፈልጉ የግብርና ግብዓቶችን ለሚያቀርበው ድርጅት ክፍያ በመፈፀም አርሶ አደሩ በሚሰጠው ኩፖን ግብዓቶቹን ከአቅራቢው ድርጅት እንዲወስድ በማድረግ ገንዘቡ ለታለመለት አገልግሎት እንዲውል የሚደረግ ነው፡፡ በሌላ መልኩ አርሶ አደሩ በባንክ ብድር ያመረተው ምርት በምርት ዘመኑ በሚከሰት ድርቅ ጉዳት ከደረሰበት ብድሩን የኦሮሚያ ኢንሹራንስ የሚሸፍንለት ይሆናል፡፡





የስልጠና ተሳታፊዎች በከፊል

# ባንኩ በተለያዩ ተቋማት አዘጋጅነት የተካሄዱ ኤክስፖና ባዛሮች ላይ ተሳትፎ አደረገ

የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በመደገፍ ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ እያበረከተ የሚገኘው አዋሽ ባንክ የተለያዩ ተቋማት ባዘጋጁት ኤክስፖ እና ባዛር ላይ ተሳትፏል።

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አዘጋጅነት ከሚያዝያ 28 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተካሂዶ በነበረው “ኢትዮጵያ ታምርት ኤክስፖ 2023 “ሀገራዊ ንቅናቄ አዋሽ ባንክ ተሳትፎ በማድረግ ዘርፉን ለመደገፍ ያለውን ቁርጠኝነት እና ሀገራዊ አለኝታነቱን አስመስክሯል።

በተመሳሳይ አዋሽ ባንክ የንግድ ትስስሮቹን መፍጠር የሚያስችለውን በአርኪ ኮንስትራክሽን ኤክስፓ አዘጋጅነት በሚሊኒየም አዳራሽ ከግንቦት 05 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለሶስት ተከታታይ ቀናት በተካሄደው አርኪ ሪልስቴት ኤክስፖ ላይ ተሳትፎ አድርጓል።

# ምልከታ

## ህልመኞቹ... እና ህልም ፈቺው...

ተፈጥሮ የራሷ የሆነ ውድ ስጦታ አላት፡፡ ለእያንዳንዱ ሰው ዕውቀትና ጥበብን ትቸራለች፡፡እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች የሰው ልጆችም ሆኑ የሌሎች ህያው ፍጥረታት አስፈላጊ ፍላጎቶችን ለማርካት ያገለግላሉ ፡፡ አንዳንዶች ተፈጥሮ የቸረቻቸውን እምቅ ዕውቀትና ችሎታ በትምህርት፣ በልምድ አዳብረው ራሳቸውን፣ ማህበረሰባቸውንና ሀገራቸውን በማገልገል የማይረሳ ታሪክ በመስራት የማይጠፋ አሻራቸውን ያኖራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በተፈጥሮ የተለገሱት ዕውቀትና ችሎታ በውስጣቸው እንደታመቀ ህልማቸውን ሳይኖሩ በውስጣቸው እንደተዳፈነ ይዘውት ያልፋሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ በተፈጥሮ የተቸሩትን ዕውቀትና እምቅ ጥበብ ወደ መሬት አውርደው ችሎታቸውን ለማዳበር ሲታትሩ በተለያዩ ማነቆዎች ውስንነት ያጋጥማቸውና ህልማቸውን ከግብ ማድረስ ተስኗቸው የሌሎችን ድጋፍና እገዛ ይሻሉ፡፡

ታዲያ አንድ ሰው የተሳካለት ሥራ ፈጣሪ ወይም አዲስና የተለየ የቢዝነስ ሃሳብ ወይም ዘዴ ይዞ የተነሣ ለመሆን፣ የያዘው ሃሳብና ሃሳቡን ተግባራዊ ማድረጊያ ገንዘብ ወሳኝ መሆናቸው አያጠራጥርም። ሆኖም፣ እነዚህ ሁለቱ ብቻ ኢንተርፕረኑ የተሳካለት የቢዝነስ ሰው እንዲሆን አያስችሉትም። ኢንተርፕረነር፣ ስኬትን መቀዳጀት እንዲችል ወይም ጉዞው ወደ ስኬት የሚገሰግስ ዓይነተኛ የሆኑ ድጋፎችና ትብብሮች ያስፈልጉታል። .

ለነዚህ ህልመኞች ህልም ፈቺው ደግሞ አዋሽ ባንክ ነው፡፡ አዋሽ ባንክ ከመደበኛው ስራ ጎን ለጎን ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ከፍተኛ በጀት በመመደብ እና ከመደበኛ ስራ ጋር በማስተሳሰር ዜጎች የተሻለ ህይወት እንዲኖራቸውና ለማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዲኖረው፡ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ልክ እንደ ወንዙ የብዙዎችን ህልም ዕውን ያደረገ፣ በረካቶችን ያበለጸገ፣ በችግር ደርቀው የነበሩ እጆችን ያለመለመ ስመ ጥር የህዝብ ባንክ ነው አዋሽ ባንክ፡፡

አዋሽ ባንክ በስራ ያምናል መልካም ውጤቶች የስራ ፍሬ ናቸው ሺ እርምጃ አንድ ተብሎ እንደሚጀመር ሁሉ የህልመኞች ህልማቸው ዕውን እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍ አንድ ብሎ በመጀመር አለኝታነቱን ያስመሰከረ ባንክ ነው፡፡



የፈጠራ ስራ ተወዳዳሪዎች በስልጠና ላይ

ባለፉት ጊዜያት የፋይናንስ አቅርቦቱ በትላልቅ የቢዝነስ አንቀሳቃሾች ላይ ብቻ ተወስኖ የነበረ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ቢዘነስ አንቀሳቃሾችም ባንኩ የፋይናንስ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ አገልግሎቱ ሁሉን አካታችና ተደራሽ እየሆነ መምጣቱን የሚያሳይና ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው፡፡

ለሦስት ዓመታት በአዋሽ ባንክ በሃሣብ ሲብላላ የነበረው ይህ የታታሪዎች ውጥን በባንካችን የዳይሬክተሮች ቦርድ መልካም ፈቃድ እ.ኤ.አ. መስከረም 2021 ላይ Packages of “Financial Products and Services for Start-ups and SMEs” የሚል Policy ይሁንታ አግኝቶ በመጽደቅ ወደ ትግበራ ተገባ፡፡

ባንኩ በማህበረሰቡ ውስጥ የስራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸው ስራ ፈጣሪዎችን ማበረታታትን ታሳቢ ያደረገ የስራ ፈጠራ ውድድር ፕሮጀክት ቀርፆ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩን ደግሞ ባንኩ ከምንም በላይ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ በሁሉም ዘርፍ አስተዋፅኦ ለማበርከት ያለው ዝግጁነት ትልቅ ማሳያ ነው፡፡

ይህ የስራ ፈጠራ ውድድር የስራ ክህሎትንና አዳዲስ ስራዎችን የመፍጠር ችሎታ እያላቸው ካለባቸው የፋይናንስ አቅርቦት ችግር የተነሳ ወደ ስራ መተርጎም ያልቻሉ ፕሮጀክቶቻቸውን እውን ለማድረግ የሚያስችል እንደመሆኑ መጠን የስራ ፈጠራ ባለቤት ለሆኑ ዜጎች በተለይም ለወጣቶች መልካም አጋጣሚ መፍጠሩ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡

በተለይ በዚህ ዘመን በሀገራችን የስራ አጥ ቁጥር እያሻቀበ በመጣበት ወቅት ባንኩ በተለይ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ቢዘነስ አንቀሳቃሾች ልዩ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ አገልግሎቶችን በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡

ሁሉም ሰው እንደሚገነዘበው ሀገራችን ኢትዮጵያ ከአፍሪካ በህዝብ ብዛት ሁለተኛ መሆኗን እና በየዓመቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት ስራ ፈላጊ በመሆኑ "የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ" እንዲሉ የስራ ፈጠራ አስፈላጊነትን ከመቼውም ጊዜ በላይ ቀዳሚ አጀንዳ ሆኖ መጥቷል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ መንግስት ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከከለኛ ቢዘነሶች ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን ተቋማቱም የማይናቅ የስራ እድል እየፈጠሩ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ተቋማት ይህንን ስራቸውን ለማከናወን ከፍተኛ የፋይናንስ ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ በተለይ ከጥቃቅን አነስተኛ እና መካከለኛ የፋይናንስ ተቋማት ወይም ከባንኮች ሊያገኙ የሚገባውን ብድር በተለያዩ ምክንያቶች ሳያገኙ ይቀራሉ፤ ከእነዚህም አንዱ የብድሩ በቂ ዋስትና ማቅረብ አለመቻላቸው ነው፡፡

አዋሽ ባንክ "ታታሪዎቹ" የተሰኘውን የሥራ ፈጠራ ውድድር ሲጀምር ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው አቅም ያላቸውና የነገ የሀገሪቱ ተስፋ ሊሆኑ የሚችሉ ስራ ፈጣሪዎችን ኮትኩቶ በማሳደግ ለሀገርና ለወገን አለኝታ እንዲሆኑ የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ ነው፡፡

በተለይ የዚህ የስራ ፈጠራ ውድድር ተካፋዮች የሥራ ፈጠራ ሃሳባቸው በሳይንሳዊና በሙያ ስልጠና እንዲጎለብት መልካም አጋጣሚ መፍጠር ነው፡፡

በውድድሩ ላይ በርከት ያሉ አመልካቾችን ለማግኘት ሲባል ባንኩ በዘረጋው የምዝገባ ስርዓት በOnline እንዲሁም በአካል ማመልከቻዎችን በመቀበል ምዝገባ ያከናወነ ሲሆን በተለይ የOnline Platform እንደ አማራጭ መቅረቡ ብዙ አመልካቾች እንዲመዘገቡ አድርጓል፡፡

ታዲያ ብዙዎችን አሳታፊ በሆነው በዚህ በታታሪዎቹ የሥራ ፈጠራ ውድድር ከሁሉም ክልሎች ከ7000 በላይ አመልካቶች በንቃት መሳተፍ ችለዋል፡፡

መቼም በውድድር መድረክ ላይ ሁሉም ተወዳዳሪ አሸናፊ ሊሆን አይችልም፡፡ መቅደምና መቀደም መብለጥና መበለጥ ግድ ይላል፡፡

አሸናፊዎችን ለመለየትም በተደረገው በአዋሽ የታታሪዎቹ የሥራ ፈጠራ ውድድር በሶስት ደረጃዎች ተከፍሎ ተካሂዷል፡፡ በመጀመሪያው ዙር 1259 የተመረጡ አመልካቾች ስልጠና ወስደዋል፡፡ በስልጠናውም ተወዳዳሪዎች የቢዝነስ ልማት ሙያዊ ስልጠና ለሦስት ቀናት ወስደዋል፡፡ ስልጠናውን በስኬት ወስደው ላጠናቀቁ ተወዳዳሪዎች ሰርተፊኬትና መጠነኛ የኪስ ገንዘብ አዋሽ ባንክ እነሆ ብሏቸዋል፡፡

## ውድድሩ ቀጠለ...

ልምድ ባላቸው ታዋቂ ግለሰቦች፣ በተሳካላቸው ስራ ፈጣሪዎች፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መምህራኖችና ተመራማሪዎች እንዲሁም አሰልጣኞች ውድድሩ የሚዳኘው ሁለተኛው ዙር ውድድር የመጀመሪያውን ዙር በስኬት አጠናቀው ወደ ሁለተኛው ዙር ያለፉ 133 ህልመኞች ልዩ ስልጠና በመውሰድ ዳኞችን ያስደመመ ብርቱ ፉክክር በማድረግ ምርጥ 20 ተወዳደሪዎችን በመምረጥ ውድድሩ ተጠናቀቀ፡፡ ስልጠናውን ያጠናቀቁ ተሳታፊዎች ጠቀም ያለ የገንዘብ እና የምስክር ወረቀት ተበረከተላቸው፡፡

## የመጨረሻው መጀመሪያ...

መድረኩ እጅግ ደምቋል፣ ዳኞችና የክብር እንግዶች ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል ጠቀም ያለ የገንዘብ ሽልማትና ሃሳባቸውን ወደ ተግባር የሚለውጡበት ስልጠናና የናሙና ማሳያና የአዋጭነት ሃሳባቸውን የሚያቀርቡበት ሰዓት ደረሠ፡፡ የመጨረሻው የፍጻሜ ውድድር 20 ተፋላሚዎች የማሸነፍ ወኔ በልባቸው ይዘው የውድድሩን መጀመር በጉጉት ይጠባበቃሉ፡፡

## ተጀመረ...

የውድድሩ ማስጀመሪያ ፊሽካ ተነፋ ፍልሚያው ቀጠለ፣ ማራኪ፣ አጓጊ እና ቀልብን በሚገዛ አቀራረብ ብርቱ ፉክክር ተደርጎ አይጠናቀቅ የለ ውድድሩ ተጠናቀቀ፡፡

ሁሉም ታዳሚ አሸናፊዎችን ለማወቅ በጉጉት እየተጠባበቀ ነው፡፡ የመጨረሻዎቹ 5 ተወዳዳሪዎች እንደየደረጃቸው ተለይተው ታወቁ። ሁሉም በአድናቆት አጨበጨበ የማይረሳ ጊዜ፡፡ በመጨረሻም የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ፀሀይ ሽፈራው እንደዚህ አሉ " ይህ የወጣቶችን የስራ ፈጠራ ሀሳብ መደገፍና ለስኬት ማብቃት የአዋሽ በጎ ተግባር በዚህ አይገታም በቀጣይ ከዚህ በተሻለ ተጠናክሮ ይቀጥላል በማለት ለታዳሚው ተናገሩ"፡፡ ህልም ፈቺው አዋሽ ባንክ ህልመኞቹ ህልማቸውን ዕውን የሚያደርጉበት ከብር 200,000 እስከ ብር 1,000,000 ሽልማት እና ከዋስትና ነፃ እስከ ብር 5 ሚሊዮን ብድር እንደየ ፕሮጀክታቸው የሚያገኙበት ስጦታ በማበርከት ቃሉን በተግባር በመፈጸም የሀገር አለኝታነቱንና የህዝብ አጋርነቱን በይፋ አስመሰከረ ክብር ይገባዋል! አዋሽ አንደኛ የሆነው በምክንያት ነው፡፡



# አርዓያ ሰብ

ታማኝነት ውድ ስጦታ ነው! ታማኝነት አያስከፍልም፣ ታማኝነት ክብሩ ታላቅ ነው፤ ታማኝነት በቃል የሚነገር አይደለም በተግባር የሚገለጽ እንጂ።

ታማኝነት ለራስ፤ ለሥራ ወይም ለሙያ፣ ለጓደኛ፣ ለተቋም፣ ለህብረተሰብ፤ ለአገር፣ ወዘተ.ለገቡት ቃል ኪዳን ጸንቶ መቆምን እና መስዋዕት መሆንን የሚመለከት ነው።

ታማኝ ሠራተኞች ደግሞ ለተቋማቸው ተልዕኮ ስኬት መሳካት አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውንም ተግባሮች በታማኝነት ለመሥራት ቁርጠኝነት አላቸው።

ታማኝነት ለታይታ የሚደረግ ወይም ጭፍን ታዛዥነት ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንስ ህጋዊ እና ትክክለኛ ለሆኑ የአገር ህጎች፣ የተቋም መመሪያዎች እና ደንበኞች ታማኝ ሆኖ በቁርጠኝነት እና በኃላፊነት ስሜት መሥራት ማለት ነው፡፡

ደንበኞቻችን አዋሽ ባንክን መርጠው ወደ እኛ ሲመጡ በቅንነት እንደምናገለግላቸው ሙሉ እምነታቸውን በእኛ ላይ አሳድረው ነውና የደንበኞችን መረጃዎች፣ ንብረቶችና ማስረጃዎችን መጠበቅ ደግሞ የታማኝነታችን መገለጫ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የባንካችንን በጎ ገጽታ ከመገንባት ባሻገር ደንበኞች በባንካችን ላይ ያላቸውን እምነት ሙሉ እንዲሆን ያደርጋል።

ነገሩ እንዲህ ነው ወርሃ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም በአንደኛው ቀን ከሰዓት በኋላ አንድ የአዋሽ ባንክ ደንበኛ የሆኑ ግለሰብ አገልግሎት ለማግኘት ወደ አዋሽ ባንክ አቃቂ ገበያ ቅርንጫፍ ያመራሉ፤ እዚያም እንደደረሱ ወደ ደንበኞች አገልግሎት በማምራት የሚፈልጉትን አገልግሎት ተስተናግደው ወደ ጉዳያቸው ያቀናሉ፡፡

ታዲያ ደንበኛው በቅርንጫፉ በሚስተናገዱበት ወቅት አጋጣሚ በደንበኞች ማስተናገጃ አካባቢ ክብደቱ 3.5 ግራም የሆነ ባለ 21 ካራት ወርቅ ጥለው ከስፍራው ይሄዳሉ፡፡

በአቃቂ ገበያ ቅርንጫፍ የደንበኞች አገልግሎት መኮንን የሆኑት አቶ ቸርነት ገመቹ ጌጡን ከወደቀበት በማንሳት በቀጥታ ለቅርንጫፉ ስ/አስኪያጅ በማስረከብ አዋሽ ባንክ የጣለባቸውን ኃላፊነት እና አደራ በመፈጸም ታማኝነታቸውን በተግባር አስመሰከሩ፡፡

መልካም ስም ከመልካም ሽቶ ይበልጣል እንደሚባለው ታማኝነት ከአንድ የባንክ ሠራተኛ የሚጠበቅ ሙያዊ ስነምግባር ነውና አቶ ቸርነት የሰሩት በጎ ተግባር ለሌሎች የአዋሽ ባንክ ሠራተኞች አርዓያ ሰብ በመሆኑ ከአዋሽ ባንክ ምስጋናና አድናቆት ተችሯቸዋል፡፡

በዘመናችን ታማኝነትን በቃል ሳይሆን በተግባር የሚያሳዩ ቅንና ታማኝ ግለሰቦች ምስጋናና አድናቆት ሊቸራቸው ይገባል፡፡ የአዋሽ ባንክ ሠራተኛ ሁሉ የአቶ ቸርነትን አርዓያ ሊከተል ይገባል፡፡

# አንድ ለመንገድ

## እፎይ!

ውጣ ውረድ ቀረ ተቆጠበ ጊዜ፤
ድካም ተከተተ የጭንቀት አባዜ፤
በቴክኖሎጂ ስራዬን አቅልዬ፤
በአዋሽ ኢ ስኩል ዘመነ ኑሮዬ፡፡
በሲሳይ(ሲስኮ)




## የማታ እንጀራ

በ5ዓመቱ አባቱ ሞተ፣ በ16 ዓመቱ ት/ቱን አቋረጠ ፣ በ17 ዓመቱ 4 የተለያዩ ስራዎቹን አጥቶ ነበር። ከ18 እስከ 22 ዓመቱ የባቡር ትኬት ቆራጭ ሆኖ ሰራ ነገር ግን አልተሳካለትም ፣ የሀገሩን መከላከያ ቢቀላቀልም ተባረረ፣ ለመማር አመለከተ አልተሣካለትም ፣ ለአንድ ኢንሹራንስ ድርጅት ግብይት ሰራተኛ ሆነ ይህም አልተሣካለትም። በ19 ዓመቱ ደግሞ ልጅ ወልዶ ነበር 20 ዓመቱ ላይ ሚስቱ ልጃቸዉን ይዛ ጥላዉ ሄደች

በአንዲት ትንሽየ ካፌ ምግብ አብሳይና ሰሃን አጣቢነት መስራት ጀመረ፣ የራሱን ልጅ አግቶ ሚስቱን ወደ ቤት እንድትመለስ ለማግባባት ቢሞክርም ሳይሳካለት ቀረ።

65ኛ ዓመት ሲሞላዉ ጡረታ ወጣ

ጡረታ በወጣ በመጀመሪያዉ ቀን የ$105 ቼክ ከመንግስት ደረሠዉ.. እሱ ግን የተረዳዉ መንግስት “ራስህን መመገብ አትችልም” እንዳለዉ ነበርና ከዚህ በኋላ መኖሩ ጥቅም እንደሌለዉ ራሱን አሣምኖ ራሱን የማጥፋት ሙከራ አደረገ....ይህም ሳይሆን ቀረ

አንድ እለት ቁጭ ብሎ ምኞቶቹን ወረቀት ላይ ማስፈር ፈለገ የፃፈዉ ግን በህይወቱ ሊያደርጋቸዉ እየቻለ ሳያደርጋቸዉ ስለቀሩ ነገሮች ነበር... የዛኔም በእርግጠኝነት ማድረግ እንደሚችለዉ የሚያዉቀዉን አንድ ነገር አሰበ...ምግብ ማብሰል

ወዲያዉ የመንግስትን የዉለታ ቼክ መልሶ $87 ተበደረ

በዚያች ብድርም ቅመሞቹን ሸምቶ ፍራይድ ችክን(የተጠበሰ ዶሮ) አዘጋጀ... እናም በኬንታኪይ ለሚኖሩ ጎረቤቶቹ በራቸዉ ድረስ እየሄደ መሸጥ ጀመረ

አስታዉሱ ይህ ሰዉ በ65 ዓመቱ ራሱን የማጥፋት ሙከራ አድርጎ ነበር!!! ግን በ68 ዓመቱ ኮሎኔል ሳንደርስ የኬንታኪይ ፍራይድ ችክን ኢምፓየር (KFC) መስራች ቢሊየነር ሆነ!!!

# PROVERBS

- Give nine, save ten. ~Iranian
- What you save is, later, like something found. ~Yiddish
- Do not be like a miser who saves for those who will bury him. ~Malagasy
- A penny saved is better than a florin earned. ~Dutch
- Why save when your son is a good son? Why save when your son is a bad son? ~Indian
- He who buys what he does not need, steals from himself. – Swedish
- Plans fail for lack of counsel, but with many advisers they succeed.
- Save three pieces of gold and the fourth one will fall into your lap. ~Croatian
- All hard work brings a profit, but mere talk leads only to poverty. ~ Dutch
- One who oppresses the poor to increase his wealth and one who gives gifts to the rich—both come to poverty.
- For age and want save while you may, no morning sun lasts a whole day. ~United States
- Go to the ant, you sluggard; consider its ways and be wise! It has no commander, no overseer or ruler, yet it stores its provisions in summer and gathers its food at harvest.

Source: https://proverbicals.com/saving-proverbs

# QUOTES

- "The more your money works for you, the less you have to work for money!" Idowu Koyenikan
- "Time is more valuable than money. You can get more money, but you cannot get more time!" Jim Rohan
- "REACH PEOPLE plan for three generations; POOR PEOPLE plan for Saturday night!"
- "Too many people spend money they haven't earned, to buy things they don't want, to impress people they don't like!"
- "Rich isn't an amount of money, it's a mindset about how you live. If you believe you can win, you can.
- "Beware of little expenses; a small leak will sink a great ship!" Benjamin Franklin

# Photo Reel





















Tatariwochu and "Qaxaleewwan" Award cermony










10th round lottery winners award program

# The LEADING

Private bank
In Ethiopia



አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

8980

www.awashbank.com